ነሐሴ10ቀን
2010ዓም

# <u>የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ!</u>

ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በሽግግሩ ፓርላማ ውስጥ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን አንድነት አሥመልክተው የኤርትራን መገንጠል በመቃወማቸው በገንጣዮቹ ጥርስ ተነከሰባቸው።አማራውን በዘሩ ለይቶ ማጥቃትንም በመቃወም መታገላቸው ለዕልፈት እንደዳረጋቸው ይታወቃል።
<u>በኢሕአዴጎች(ትህነግ፣አህዴድ፣ብአዴንና ድህዴን)</u> ለ27ዓመታት "ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ አንድነት" እንደወንጀል ተቆጥሮ ኖሮ ከአራት(4) ወራት ወዲህ በዚያው <u>በኢሕአዴግ ሥርዓት ውስጥ በመጣ ጠቅላይ ሚኒስቴር</u> በዶክተር አቢይ አህመድ አንደበት ሲነገር፣<u>አዲስ ባይሆንም</u>፣አገርና ሕዝብ ምሥቅልቅሉ ወጥቶ ተሰፋ ለቆረጠው ሕዝብ ግን <u>እንደአዲስ ሆኖ፣</u> አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሠንደቅ ዓላማ ይዞ በመሰለፍ ሞቅ ያለ ድጋፍ አሥገኝቶለታል።

ዶክተር አቢይ የኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሆነበት ቀን ጀምሮ ዱሮም ወንጀል ያልሰሩ መታሰር የማይገባቸው ቢሆኑም የታወቁትን ከእሥር አሥፈትቷል።እርግጥ ዛሬም ቢሆን ብዛት ያላቸው አማሮች በትግሬ እሥር ቤቶች እና በአጠቃላይ በአገሪቱ ከአማራውም በተጨማሪ የሌሎችም ወገኖች እሥረኞች አልተፈቱም።ሌላው ከኤርትራ ጋር ሠላም ፈጥሯል፣ቤተ ክርስቲያንን አሥታርቋል፣ለጊዜው ሕዝቡም ትንሽ ለመተንፈስ ችሏል ወዘተ።በተቃራኒው ደግሞ በየቦታው ለ27ዓመታት የዘለቀው የዘር ግጭት ቀጥሏል።ይህ ማለት አገር የበተነው ህገ መንግሥት ሳይነካ እየተሸሞነሞነ እሥከቀጠለ ድረስ የዶክተር አቢይ ለውጥ መሠረታዊ ሳይሆን ጥገናዊ ነው ማለት ነው።

ዛሬ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ|ር አቢይ የሚመራው የአራቱ <u>የትህነግ፣የአህዴድ፣የድህዴን</u>ና <u>የብአዴን(ኢህዴን)</u> የዘር ድርጅቶች ጥምረት <u>ኢሕአዴግ</u> ከሌሎች የዘር ድርጅቶች ጋር በመሆን ፣አማራ ባልተካፈለበት በ1983ዓም የሽግግር ወቅት **<u>የኢትዮጵያን አንድነት አጥፍቶ በዘጠኝ(9) የዘር ክልሎች በመተካት</u>** ዛሬ ያለውን ከፋፋይ ህገ መንግሥት ማፅደቁ ይታወሳል።ዶክተርአቢይ!ዕርቅን፣ እንደመርን ሠላምን፣ፍቅርን፣ኢትዮጵያዊነትንና አንድነትን የሚሰብከው በዚሁ ህገ መንግሥትና የዘር ድርጅት ውስጥ ሆኖ ነው።

ከ1983ዓም ጀምሮ <u>በቀጥታ</u> የነጮቹ ጣልቃ ገብነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቅድሚያ ሳልጠቅስ የማላልፈው ነገር ቢኖር ዶክተር አቢይ ጠቅላይ ሚኒስቴር የሆነው በትነግ ትግሬዎችና በኦሕዴድ ኦሮሞዎች መካከል በተደረገው የሥልጣን ትግል በኦሕዴድ ጊዜያዊ አሸናፊነት እንደሆነ ይታመናል።እንደሚታወቀው አማራው ከትነግ ጎን ቆሞ ደርግን ተዋግቶ ትነግን ሥልጣን ካቆናጠጠ በኋላ በትነግ ተከድቶ 27ዓመት ሙሉ ይቀጠቀጣል።ዛሬ ደግሞ አማራው ኦሕዴድን አጅቦ ሥልጣን ሲያቆናጥጥ በእነኦነግ እየተሳደደ ይገኛል።ነገ የከፋ አደጋ እንዳይመጣበት <u>መፍትሄው</u> ከአሁኑ ፈጥኖ መደራጀትና መመከት ብቻ ነው።

*መታወቅ ያለበት ግን አቢይን ወደሥልጣን ያመጣው <u>ከአቢይ ሥልጣን በላይ፣ሥልጣን ያለው የትነግ|ኢሕአዴግ ድርጅቶችና ህገ መንግሥታቸው</u> ነው ።ይህ ከአቢይ በላይ ሥልጣን ያለው መዋቅር ደግሞ እሥካልተወገደ ድረስ ወይም የአቢይ ቡድን*

በትነግ|ኢሕአዴግ ውስጥ እሥካሁን እንደሚያደርገው ጥገናዊ መሳይ አካሄድ ሳይሆን መሠረታዊ ለውጥ እሥካላየን ድረስ፣ ይዋል ይደር እንጅ 27ዓመት ሙሉ ሕዝብን በጅምላ ሲገድል፣ሲያስር የኖረው ህገ መንግሥትና ድርጅት እንዳሁኑ ተዘናግተን ካየነው ተጠናክሮ መቀጠሉ አይቀሬ ነው። በነገራችን ላይ ዶክተር አቢይም አሜሪካ ላይ በጭብጨባ ያደነቀረውንና የደገፈውን ማህበረሰብ የፖለቲካ ንቃት ከገመተ በኋላ እንዲህ ሲል አፈረጠው፣"ኢሕአዴግ ተዳከመ የሚሉ ሰዎች ተሳስተዋል፣ኢሕአዴግ እንዳሁን ተጠናክሮ አያውቅም" ነበር ያለው።ይህ ተቃዋሚውን ዕርቃኑን ያሥቀረ ፣ጊዜያዊም ቢሆን ትልቅ አደጋ ነው።በቅንጅት ጊዜ እንደታዬው፣ከተወሰኑ ወራት በኋላ ያው እንደጥንቱ መሆኑ አይቀሬ ነው።

ዶክተር አቢይ አህመድ የጠቀሳቸው "ኢትዮጵያ፣የኢትዮጵያ አንድነት፣ፍቅር" ማራኪ ናቸው።ነገር ግን ዕርቁና መደመሩ ከማን ጋር ነው? አገሪቱንና ሕዝቧን ሆን ብለው ዛሬ ወደምንገኝበት ምሥቅልቅል ሁኔታ ላይ የጣሉን ሥለእርቅም ሆነ ሥለመደመር ቢጠቀስም የማይቀበሉት ዛሬም ድረስ እየገደሉን ያሉት የትነግ ትግሬዎችና የኦሮሞ ኦነጎች ናቸው። "ቀኝህን ሲመታህ ግራህን ሥጠው" ዓይነት አካሄድስ እሥከመቼ?አማራው አሥብበት!!!

ይህ ዛሬ ያለው "ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ህገ መንግሥት ከዘርና ከቋንቋ ክልሎች ጭምር እሥካልተለወጡ ድረስ ፣ትናትናም ሆነ ዛሬ እያመሱን የሚገኙት የይገባኛል ጥያቄዎች ሲያጋድሉን ይኖራሉ።
"አንድ ቦታ እሳቱ ቢበርድ፣ሌላ ቦታ እየተቀጣጠለና ሁኔታው እያገረሸ "የኔ ፣የአንተ" በሚሉ የዘር ክልል አባዜዎች በመወጠር መገዳደሉንና መፈናቀሉን ለማስቆም ዶክተር አቢይ ጊዜያዊ እንጅ ዘላቂ መፍትሄ አይኖረውም።

ይህ ዛሬ የሚታየው ከመናገር ያላለፈ፣ጥገናዊ ለውጥ መሳይ "ሰበር ሰካ" አካሄድ፣ከኤች አር 128 እና ከሌሎች የትግል መንገዶች ጭምር ነጩም ዓለም ሳይቀር ትነግ|ኢሕአዴግን በመቃወም ከጎናችን መሆን ሲጀምር፣የተቀጣጠለውን የሕዝብ ዕምቢተኝነት ትግል በተወሰኑ ጣፋጭና ውብ ቃላት፣ "ተቃዋሚ ነኝ" ይል የነበረው የህብረተሰብ ክፍል በሚገርም ሁኔታ እጅ በመሥጠቱ፣ሊመክኑ ቻሉ።ሥንት ግብግብ ሲደረግ ኖሮ፣ሥንት ነፍስ አልቆ፣ትግሉ ጠንክሮ ነፍሰገዳዩ ትነግ|ኢሕአዴግ ሊወድቅ ሲንገዳገድ ነፍስ እንዲዘራና ሠቆቃችን እንዲራዘም ሆነ።ትግሉ ላይ ውሀ ተቸለሰበት።

ምናልባት ይህ የኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት ወርቃማ ንግግሮች፣አማራው የተገለለበትን፣ "በኢትዮጵያን አንድነት መቃብር ላይ የተሸነሸኑትን የዘር ክልሎችና የዘር ህገ መንግሥት ተብየዎቹን ሳይሸራረፉ በአንድነት ንግግርብቻ ለማስቀጠልና የነበሩትን የሕዝብ እንቅስቃሴዎች ለማዳፈን ታስቦ ከሆነ ተቀባይነት የለውም።
**ዛሬ ዶክተር አቢይ የሚጠራው "የኢትዮጵያ አንድነት" ዕውን የሚሆነው በ1983ዓም የኢትዮጵያን አንድነት የናደው፣ዛሬ ድረስ በህይወት ያለው "ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገው ህገ መንግሥት ከዘርና ቋንቋ ክልሎች ጭምር ፈርሶ፣ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተዋቀረ በደንብ የተጠና፣ከዘርና ከቋንቋ ነፃ የሆነ ለአሥተዳደር የሚመች በጥልቀት የተጠና የተለያዩትን የአካባቢያዊም ሆነ ሌላ ዓይነት ፌደራሊዝምን ባካተተ ህገ መንግሥት ሲተካ ብቻ ነው።**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ በገዛ አገሩ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ በየትናውም አካባቢ የመሥራትና የመኖር ብሎም የመናገር መብቱ በአጠቃላይ  የግለሰብ ነፃነቱ መከበር የግድ ነው።**
**እነኚህ ተግባራዊ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ አንድነት ዕውን እንደማይሆን ለማንም ግልፅ መሆን አለበት።**

ሥለዚህ ዶክተር አቢይ ፍቅርን፣ሠላምን፣ኢትዮጵያዊነትንና የኢትዮጵያን አንድነትም ያካተቱ  ውብ ቃላትን ተጠቅሞ ፣ጥገናዊ ሳይሆን ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት፣ከሁሉ በፊት ትነግና አነግ ያደረጉትን የዘር ሸንሸና  ሀ)ህገ መንግሥት ተብየውን ማሥወገድ  (ለ) የቋንቋና የዘር ክልሎችን ማፍረስና  በጥልቀት ውይይት  በተጠኑ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያቀራርቡና የሚያስማሙ፣እኩልነትንም የሚያሟሉ አካባቢያዊም ሆነ ሌላ ዓይነት ፌደራሊዝም  በቅድመ ሁኔታነት መቀመጥ ሲችል፣ ሙሉ ድጋፋችንን ያገኛል።  ዛሬ ከቃላት በሥተቀር የተጨበጠ ነገር ሳይኖር መደገፍ ነገ ማጣፊያው ይቸግራል።

**ማስታወሻ!** ዛሬ ያለው ህዝብን ከህዝብ ሲያጋድሉ ዛሬ ጋ የደረሡት፣ህገመንግሥትና የዘር ክልሎች የተፈጠሩት አማራው በተገለለበት በመለስ ትነግና በሌንጮ አነግ ወሳኝነትና ማናለብኝነት  ሥለሆነ አማራው አይቀበለውም።

**ያም ሆነ ይህ  ዛሬ ዶክተር አቢይ የሚለው  ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት ከቃል ያላለፈ ጥገናዊ ለውጥ ዓይነት ቢሆንም እንኳን፣**

(1)በተለይ  ሁኔታው  ለአማራው  የመደራጀት  በር  ሥለከፈተ፣አማራው  ከአብን  ጭምር የተገኘውን ቀዳዳ በመጠቀም ይትጋ።በተለያዩ ቦታዎችም እየሄደ  አማራውን ያንቃ እላለሁ።

(2)ከታክቲክ አንፃርም  ለአማራው የህልውና ጥያቄ ጥቅም አለው።ምክንያቱም  አማራው ባልተሳተፈበት በ1983ዓም ኮንፈረንስ አማራውን አጣብቂኝ ውስጥ አሥገብተው ርስት አልባና ተባራሪ ያደረጉት፣"የኢትዮጵያ አንድነት" የሚለውን ቃል የሚጠሉት፣ከአቢይም ያፈነገጡ የሚመሥሉት፣ የዝሆኑን ድርሻ መሬቶች የወሰዱት ትነግና አነግ ዛሬም ድረስ  አንድነቱን አይቀበሉም።ከተቀበሉ ግን የሠረቋቸው መሬቶች ወደባለቤቶቹ ይመለሳሉ።ለዚህም ነው ዛሬም ድረስ በአማራ ላይ ግድያ ከመፈፀምም አልፈው በጠቅላላ በአገሪቱ ውስጥ ቀውስ የፈጠሩት።

ምንም ተባለ ምን  ወደዋናው  መፍትሄ ሥንጓዝ "ይህች ዓለም የምታጅበው ጉልበት ያለውን ብቻ እንደሆነ ተረድተን"  አሁን የጀመርነውን መሰባሰብ ይበልጥ በማጠናከር፣ ያልሞከርነው የትግል አካሄድ ካለ በመቃኘት፣የድርሻችንን ለማግኘት  በተለያዩ የትግል መንገዶችና ዘዴዎች  ተጠናክረን   መብታችንን በእጃችን ማድረግ የግድ ነው።

ሥለዚህ እንደአማራ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሥቀመጥ ግድ ይለናል፣
(ሀ) ዛሬ ያለው "ህገ መንግሥት" አማራ ያልተሳተፈበትና አማራን የማይወክልም አማራን ያገለለና በአማራ ላይ የተጫነ  በመሆኑ፣

(ለ)የኢትዮጵያን አንድነት አፍርሶ ቋንቋንና ዘርን መሠረት ባደረጉ 9የክልል መንግሥታትና ባንዲራዎች የከፋፈለና እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ የእርስ በእርስ መናቆርን የተከለብን በመሆኑ፣

(ሐ) በአድዋም ሆነ በተለያዩ የአገር ሉዓላዊነት ጦርነቶች የነጭንም ሆነ ሌሎች ተስፋፊዎችን ታግለን አገራችንን ያሥከበርንበትን ሠንደቅ ዓላማ የሀሰት ትርጉም ሰጥቶ በመጣል፣ የብሄረሰቦችንና የሀይማኖቶችን እኩልነት የሚገልፅ በሚል ቅጥፈት ሌላ ባንዲራ ማድረጉ አግባብነት ሥለሌለው፣ሠንደቁ ወደቀደመው ክብሩ እንዲመለስ፣(መ) በንጉሳዊያን ላይ በተለይ ደግሞ በአፄ ሚኒልክ ላይ በመዝመት ከባርነት ነፃ ያወጣቸው ሰንደቁም እንደጨቆናቸው የሚተርኩት፣በመጀመሪያ ደረጃ የንጉሳዊያን ሠንደቅ እላዩ ላይ አንበሳ ያለበት ነበር። ይህ ምልክት የሌለው ሰንደቅ ዓላማ የሕዝብ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት አንበሳ ያለበትን የቤተ መንግሥቱን በአደባባይ አውጥተው ለሕዝብ እሥካደረጉበት ጊዜ ድረስ፣ይህ መሃሉ ምልክት የሌለው የሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ እንደሆነ ግልፅ ነው፣

(ሠ)የቋንቋንና የዘርን ክልል ፌደራል አወቃቀር አፍርሶ በጥናት ላይ የተመሠረተ ፌዴራሊዝም በማዋቀር አብሮነታችንን ማጠናከር።

ይህ አማራው የሚጠቀምበት እንጅ የሚጎዳበት ሥለማይሆን ሁሉም የአማራ ድርጅቶች ተሰባስበው በአንድነት በመቆም በአናሳ ጎሳዎች ጭምር ተንቆ መሬት ላይ ወድቆ የሚፈራገጠውን የአማራ ወገናችንን እንታደገው ዘንድ እማፀናለሁ።
በመሆኑም ዛሬ አገር ቤት የተፈጠረውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ውስጥም ውጭም የሚገኙ የአማራ ወገኖች ቅድሚያ ሠጥተው በአፋጣኝ እንዲተባበሩ ነባራዊ(ተጨባጩ) ሁኔታው የግድ ይላቸዋል።

በመከባበር-በመደማመጥ-በመማማር የአማራው ህልውና ይረጋገጣል!

አያሌው ፈንቴ

—